# ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

## ንዋያተ ቅድሳትና አያያዛቸው


*ከሂሩት ገብረሂዳን*
/አ.አ.ዩ.ኢንፎርሜሽን ሳይንስ ዲፓርትመንት/


ባለፈው እትማችን የዜማና የማኅሌት መገልገያ ንዋያተ ቅድሳትን በዝርዝር መመልከታችን ይታወሳል:: በዚህ እትማችን ደግሞ የቤተመቅደስ መገልገያዎችን እንመለከታለን::

ጻሕል/ልሳን/

የኅብስቱ ማስቀመጫና ማክበሪያ ነው:: ይኸውም ከወርቅና ከብር ከናስና ከብረትም የሚሠራ ነው:: የተለየ ቅርጽ የተለየ ምልክት ያለው ነው:: ምሳ. 25÷11::

ጻሕል – የእመቤታችን የማኅፀኗ ምሳሌ ነው:: እንዲሁም ጻሕል ክርስቶስ የተወለደበት ግርግም /የገፈራ ማስቀመጫ/ ወይም የበረት ምሳሌ ነው::መጠቅለያው /ማንፈዱም/ ክርስቶስ ሲወለድ የተጠቀለለበት ጨርቅ /ቅጠል/ ምሳሌ ነው:: በተጨማሪም ጻሕል የመቃብሩ ምሳሌ ሲሆን ማዕፈዱ ደግሞ የመግነዙ ወይም የሰንዱኒው ምሳሌ ነው:: «አንበርን ዲበ ዝንቱ ጻሕል በአምሳለ መቃብር» ይላልና::

እርፈ መስቀል : እርፈ ከሚለው ቃል የመጣ ነው:: ትርጉሙም ጨለፈ፣ ጠለቀ፣ ቀዳ ማለት ነው:: ስሙም እርፈ መስቀል የተባለው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያፈ ሰሰው ደሙ ስለሚሰጥበት ነው:: እርፈ መስቀል እንደ ማንኪያ ዓየነት የሆነ ዕቃ ነው:: ይህም ጽዋው ከተሠራበት ቁስ የሚሠራ ሲሆን በደሙ ማቀበያ በኩል በጣም ጎድጎድ ያለ ልዩ ቅርጽም ያለበት ሲሆን ከወደ እጅ መያዣው በኩል መስቀል ያለበት ነው:: ኢሳይያስ ከለምጹ የነጻበት ፍሕም መያዣ ጉጠት ምሳሌ ነው:: ኢሳ. 6÷6:: መጽሐፈ ቅዳሴ ንባብና ትርጓሜ ገጽ 31 ቁጥር 28–30::

አውድ - በድርገት ጊዜ ጻሕሉ የሚቀመጥበት ሰፋ ያለ እንደ ትልቅ ትሪ ያለ ነው:: ቅዱስ ሥጋውን እንዳይነጥብ /እንዳይወድቅ/ መጠበቂያና ሰፋ፣ ጉላም፣ብሉ እንዲታይ ለማለት የተደረገ ነው::እርሱም የሚሠራው ከብረት፣ ከነሐስና፣ ከእንጨት ነው:: ስሙ እንደሚያመለክተን አደባባይ ማለት ስለሆን የጲላጦስ አደባባይ ምሳሌ እንደሆነ ይነገራል::

### አጎበር

በአውድ ላይ የሚደፋ አራት ማዕዘን ሦስት እግር ያለው እንጨት ወይም ብረት ሊሆን ይችላል:: ይህም ሥጋውን ልብሱ እንዳይነካው ከፍ አድርጎ ልብሱን የሚይዝ የሚከላከል ነው:: እንዲሁም መጐናጸፊያውን ጎበብ አድርጐ ይዞ ክብር የሚሰጥ ነው:: ሦስት እግር መሆኑ የሶስትነት ምሳሌ ነው:: የማህተመ መቃብር ምሳሌ ነው::

### ማህፈዳት

አምስት የሚሆኑ የልብስ እራፊዎች ናቸው:: አንደኛው ከጻሕሉ ሥር ይነጠፋል:: ሁለተኛው ከጻሕሉ ላይ ይነጠፋል:: ሦስተኛው ሥጋው ይጠቀለልበታል:: አራተኛው የጽዋው ልብስ ይሆናል:: አምስተኛው ለአውዱ ልብስ የሚሆን ነው:: ሌላው ደግሞ አንዱ ከአውዱ ላይ ይነፀፋል:: ከአውዱ ላይ የሚነፀፈው ልብስ የእመቤታችን የድንግልናዋ ምሳሌ ነው::አንዱ ከጻሕሉ ላይ ይነፀፋል:: ይህ ደግሞ የሰፋድል/ሕፃን ልጅ ሲወለድ ከማሕፀን ለብሶት የሚወጣ የሥጋ ክርታስ/ ምሳሌ ነው:: ሦስቱ ደግሞ በአጎበሩ ላይ በሦስቱም በኩል ይለብሳል:: ይህ ደግሞ በሥላሴ ይመሰላል አብ ለማጽናት፣ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋ ለመልበስ፣ መንፈስ ቅዱስ ለማንፃት፤ የታችኛው ማሕፈድ ማለትም አውድ እና ጻሕል ላይ የተነጠፉት የመግነዝ፣ በላይኛው/በአጎበር/ ላይ የተነጠፉት የሰበን ምሳሌ ናቸው:: አጎበር የማኅተመ መቃብር ምሳሌ ነው:: ከመጽሐፈ ቅዳሴ ንባብና ትርጓሜ ውስጥ ሥርዓተ ቅዳሴ ምዕ.4 ገጽ 29 ቁ.15::

### መሶበወርቅ

ማለት ከቤተ መቅደስ የተዘጋጀውን ኅብስት ማምጫ ነው:: አሠራሩም በአሪት ጊዜ ለሙሴ እግዚአብሔር ያዘዘው ሽምሽር ሰጡን ከሚባል ከማይነቅዝ እንጨት ሲሆን መሶበወርቅ ቅርጽ አለው:: ይህንን በውስጥም በውጪም በወርቅ ለብጠው አለው:: እንግዲህ መሶብ የእመቤታችን፣ ወርቅ የእመቤታችን የቅድስናዋ የንጽሕናዋ ምሳሌ፣ መናው የአማናዊው የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው:: ከመጽሐፈ ቅዳሴ ንባብና ትርጓሜው ውስጥ ሥርዓተ ቅዳሴ ም. 4 ገጽ 31 ቁ. 37::

### ሙዳይ

የሚሠራው ከስንደዶ ነው:: አገልግሎቱም ለእጣን ማስቀመጫ ሲሆን፣ ሙዳዩ የእመቤታችን ምሳሌ ነው:: እጣኑ ደግሞ ምዑዝ ባሕርይ የክርስቶስ ምሳሌ ነው:: በቅዳሴ ሰዓት ከሙዳይ ውስጥ አምስት ቆቆር እጣን ይመረጣል፤ አምስቱም የአምስቱ ኪዳን ምሳሌ ናቸው:: የቁርባነ አቤል፣ የመሥዋዕተ ኖኅ፣ የሂሩተ አብርሃም፣ የመብአ ይስሐቅ፣ የተልእኮተ ሙሴ ወአሮን ነው:: የሂሩተ አብርሃም እና የመብአ ይስሐቅ አንድ ወገን ይሆንና የመስዋዕተ መልከጼዴቅ እንደ አንድ ይቆጠራል:: መጽ. ቅ. ን. ት. ገጽ 32 ቁ.21::

### ጽንሐሕ

ዕጣን ማጠኛ ማለት ነው በኦሪቱ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ሽምሽር ሽጢን ከሚባል ከማይነቅዝ እንጨት ቁመቱ ሁለት ክንድ ስፋቱ አንድ ከስንዝር ቅርጹ ከንዳበን ሙሉ እንደ ሙቀጫ ፈልፍለህ በአፍአ /በውጭ/ በውስጥ በወርቅ ለብጠው አራት ቀለበት ሁሉት ሙሉጊያ አብጅለት:: በግራና በቀኝ ሁለት አቅርንት አውጣለት ስንደርስ የሚባል ነጭ ዕጣን ፈጭተህ አኑር:: ከዚህ በኋላ ፍሕሙን አግብተህ ዕጣኑን አድርገህ በወቅር ዘንግ አዋሕደህ ጢስ ቅታሬው አምሮ እንዲወጣ ወርቁን እንዳይሰማው ፈጥነህ በብረት ጽፋው ብሎ አዝዞት ነበር:: ዘጸ.30÷6–10፣ዘጸ.37÷25.29 ይኸው ምሳሌ ነው:: ማዕጠንት የእመቤታችን፣ ወርቁ የንጽሕናዋ፣ የቅድስትናዋ፣ ዕጣን የትስብእት፣ ፍሕም የመለኮት፣ የወርቅ ዘንግ የመንፈስ ቅዱስ የከፈለ፣ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና:: አቅርንት የሥልጣን እግዚአብሔር ምሳሌ ነው::

በሦስት ዘንጐች መሐል ያለው ዘንግ ብቻውን መሐል ሆኖ ከላይ ወደታች ይወርዳል፣ ከታች ወደ ላይ ይወጣል:: ይህ ዘንግ ያንድነታቸው፣ ከጫፉ ያለው መስቀሉ በመላእክት ዓለም ያለው የብርሃን መስቀል፣ ዘንጉ ከላይ ወደታች መውረዱ ከሰማያት ወርዶ የመወለዱ፣የሞቱ፣ ወደላይ መውጣቱ የትንሣኤውና የዕርገቱ ምሳሌ ነው:: ተመልሶ ወደታች መውረዱ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሐደው ሥጋ ዳግመኛ ለፍርድ የመምጣቱ ምሳሌ ነው:: በአጠቃላይ የማዕጠንቱ ሥርዓት ርደቱን፣ ዞሮ ማስተማሩን፣

መስቀሉን፣ መቀበሩን ትንሣኤውንና ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን የሚያጠ ቃልል ነው።።

ብረት ከላይ ወደታች የሚወ ርድ ሦስት ሽቦዎች አንዱ ብረት መሆ ኑ የሥላሴ አንድነት፣ ሦስቱ ሽቦዎች የሦስትነት ምሳሌ ናቸው።። አንድነት በሦስትነት፣ ሦስትነት በአንድነት መኖ ሩን በሚገባ ይገልጻል።። ይህንን መያዝ የሚገባቸው ቀሳውስቶች ብቻ ናቸው፤ ዲያቆናት መያዝ አይገባቸውም።።

ሻኩራዎች አሏቸው የሻኩራዎቹ ብዛት ቢያንስ አሥራ ሁለት ቢበዛ ሃያ አራት መሆን አለበት።። አሥራ ሁለት መሆኑ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ሲሆን ድምፁ፣ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳትህቸ ውጣ ብሎ በተናገረው ትንቢት የሐዋር ያት ስብከት ከዳር እስከ ዳር የመሰ ማቱ ምሳሌ ሠነው።። ድምፁ በየሰዓቱ መስማቱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የማመስገናቸው ምሳሌ ነው።። አንድም የሻኩራሀዎች ድምፅ ሐዋርያት ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ናት ብለው የማስተማራቸው ምሳሌ ነው።። እዚህም ላይ ማዕጠንት ወይም ጽንሐሕ የእመቤታችን፣ እጣኑ የትስብ ዕት ምሳሌ ነው።።

እጣን እና እሳት የሚዋሐዱ በት ሙዳይ የመሰለ ነገር ክዳን አለው በክዳኑ ላይ መስቀል አለው ይህም የቀራንዮ ምስቀል ምሳሌ ነው።። በተጨ ማሪ ክዳኑ የጢስ መውጫ ቀዳዳዎች አለው ይህ የቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ነው።። እሳቱ ሰዎችን እንዳያቃ ጥላቸው በጽንሐሕ ውስጥ አስቀምጠው ዕጣኑን ያጥኑበታል።። እንዲሁም ወላ ዲተ አምላክ በማሕፀኗ መለኮትን ስትሸከም መለኮትነቱ አላቃጠላትም የፍሕሙ ማስቀመጫ ሙዳይ የመሰለ ነገር ከሶስቱ ሽቦዎች ጋር መያያዙ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ለመወለዱ በማሕፀኗ ሲያድር እግዚአብሔር አብ ሊያፀናት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሊጠብቃት በእርሷ የማደራቸው ምሳሌ ነው።። ሉቃ1÷35።። ፍሕም የመለኮት ምሳሌ ነው።። በቤተክርስቲያን ዕጣን ሲታጠን ሰርከ ሌሊትና ሰርከ መእልት ሰርከ ዕለት፣ ሰርከ ወርኅ ይታወሳል።።

ጽንሐሕ ከወርቅ ከብር ከብረት ይሠራል።። አራቱ ገመዶች የአራቱ ወን ጌላት ምሳሌ ናቸው።።

## ቃጭል/መረዋ/

_በቅዳሴ ጊዜ ቃጭል የሚደወ ለው መጥምቁ ዮሐንስ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ..» ያለው በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ ምሳሌ ነው።። ማቴ.3÷1–2።። አገልግሎቱ ቅዳሴ ሲገቡ መግባታቸውን ለማሳወቅ በቅዳሴ ጊዜ ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን ሲባል ዲያቆኑ ሲያውጅ ያላመኑ እንዲሰሙ እና እንዲወጡ፤ ከዚያም በእ ግዚአታ ላይ እያሉ ቃጭል ይቃጨ ላል።። ድርገት ሲወርዱ ይቃጨላል በተጨማሪ ለፀሎተ ምህላ እግዚአ ሲባል ይቃጨላል።። አሠራሩም ከነሐስ፣ ከብር፣ ከሌሎችም ብረት ነክ ነገሮች ነው።።

## ደወል/መጥቅዕ/

አገልግሎቱ ካህናት ሌሊት ለአገልግሎት እንዲወጡ መጥሪያ ነው።። ለምሳሌ ሌሊት ሲደወል መዘምራን ለማኀሌት፣ ሰሞነኛ ለሰዓታት፣ የጾም ቀን ሲሆን ደግሞ ስድስት ሰዓት ላይ ተጋብኡ ተብሎ ይደወላል።። ሌላው ደግሞ ከቅዳሴ በፊት ምዕመናንን ለማንቃቃት አምስት ጊዜ ይደወላል።። ይህ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌ ነው።። ወደ ፍሬ ቅዳሴ ከመግ ባት አስቀድሞ ዲያቆኑ«ፃኡ»/ውጡ/ ሲል ሦስት ጊዜ ይደውላል።። የሥላሴ ምሳሌ ነው።። በቅዳሴ ጊዜ «እግዚኦ» ሲባል በኃይለ ቃሉ መግለጫ ሆኖ አሥራ ሁለት ጊዜ ይደወላል።። የደወል ድምፅም ይሰማል።። ይህም በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስብከት ሁሉም የአንድን የጌታን ቃል/ወንጌልን/ ለማስተማራቸው ምሳሌ ነው።። ድርገት ሲወርድ ሰባት ጊዜ ይደወላል።። ይህም የሰባቱ ምሥጢራት ቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው።።። በአጠቃላይ ደወል የቅዱሳን ነቢያት ትንቢት ምሳሌ ነው።።

## ስን/መቁረሪት/ /ኩስኩስት/

ከመዳብ፣ ከነሐስ፣ ከብርና ከመሳሰሉት ይሠራል።። አገልግሎቱም በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ እጁን ሲታጠብ ለውኃ ማንቆርቆ ሪያ እና ለቅዳሴ ፀበል መያዣ እና ማደያ ሲሆን ዓይነቱ እንደ ማንቆር ቆሪያ ነው ምሳሌነቱም ጌታችንን በሰቀ ሉት ጊዜ ጲላጦስ «ንጹሕ አነ እም ደሙ ለዝብዕሲ...» ብሎ እጁን የታጠ በበት ሲሆን በፀሎተ ሐሙስ ዕለት ደግሞ የሐዋርያትን እግር ያጠበበት የጥምቀት ምሳሌ ነው።። ማቴ.27÷24 ፣ ዮሐ. 13÷5።።

## ብርት /መታጠቢያ ሳህን/

አገልግሎቱ ለእጅ መታጠቢያ ነው።። ከነሐስ እና ከሌሎች ብረቶች ይሠራል።። ቀሳውስቱ ወደ አገልግሎት ወይም ወደ ቅዳሴ ሲገቡ እጃቸውን የሚታጠቡበት ነው።። በሌላ በኩል ደግሞ እኔ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁሕ ነኝ ብለው የሚ ታጠ በበት ምሳሌ ነው።። ማቴ.27÷24።።

## መቅረዝ/ተቋም ማኅቶት/ /ተቋመወርቅ/

እግዚአብሔር ሙሴን መክሊተ ወርቅ ሀን አምጥተህ ተቅዋምን ሥራ አለው።። ከታች እንዳይፈነገል እንደ ጽዋ እግር አውጣለት።። ከዚያ በላይ አንድ መሸ ቢያ ቃትተህ ተወው ከዚያ በላይ በሦ ስት መሾቢያ ሰባት አዕፁቀ አውጣ ለት።። ሦስቱን በወዲህ ሦስቱን በወዲያ መካከለኛውን ሥረወጽ አድርገው ሰባት ሰባት ምንባረ ፈትል አብጅለት፤ በመ ካከለኛው የተቀዳው ዘይት በስድስቱም ሁሉ እንዲሞላ አድርገው ለዚህ ማፈኛ መኮስተሪያ ወለባ አብጅለት አለው።። ዘፀ.25÷31–40፣ 37÷24፣ ዘኁ.8÷4።። ይኸውም ምሳሌ ነው።። ተቅዋም የዘመን ምሳሌ ከታች እንደ መሸቢያ ቃትተህ ተወው ያለው በዘመነ አበው መጽሐፍ አልተጻፈም፤ ከዚህ በላይ ሦስት መሸ ቢያ ሰባት አዕፁቀ አውጣለት ያለው በሦስት ክፍለ ዘመን በዘመነ መሳፍ ንት፣ በዘመነ ነገሥታት፣ በዘመነ ካህናት የተጻፉ መጻሕፍት በመካከለ ኛይቱ የወንጌል ምሳሌ አዕፁቀ የሰብአ ሥላሴ፣ የሐዋርያትና የመምህራን ምሳሌ አዕፁቀ የሚያሳይ ብርሃኑ ነው።። የመጽሐፍትን ምሥጢር የሚገልጹ መምህራን ናቸውና።። ውዳሴ ማርያም ዘ ሰንበት።።

እንግዲህ መቅረዝ የመብራት መስቀያ ነው።። በብሉይ ኪዳን ከቤተ መቅደስ ዕቃዎች አንዱ ነበር።። ማቴ. 5÷15 ዘፀ.40÷24 ከን.26÷35 ዕብ. 9÷2 መቅረዝ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው።። ራእ. 1÷20 ቅርንጫፎቹ ሰባት መሆናቸው የፍፁምነት ምሳሌ ነው።። ሰባት በዕብራውያን ፍፁም ነውና።። ምሳ.24÷16 መቅረዝ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ይመሰላል ጨለማን የሚያስወግድ እውነተኛ ብርሃንን አስገኝታልናለችና እንዲሁም በማህፀኗ ተሸክማዋለችና።። ዮሐ.1÷4–9 ዮሐ.9÷5።። በቤተክርስቲያናችንም ተቀ ዋም ማህቶት መቅረዝ አላት ተቅዋመ ወርቅ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም፣ እሳት የመለኮት፣ ፈትል የት ስብእት፣ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።። በቤተክርስቲያን አዘውትሮ የሚበ ራው ጧፍ ወይም ሻማ ሲሆን እነዚህ የመላእክት መሳሌዎች ናቸው።።

## አትሮኖስ

የማሠራውም ዘንጉ ከብረት ሆኖ ከላዩ ያለው የለፋ ቆዳ አንዳንድ ቦታ ከሸንበቆ፣ ከመቃ፣ ከቀርከሀ ይሰራል።። አገልግሎቱም መጻሕፍት ይዘረጋ በታል።። በተለይም የዜማ መጻሕፍት፤ ምሳሌነቱም የእመቤታችን የማሕፀኗ ነው።።

## ማኅደር

የመጻሕፍት ማስቀመጫ ሲሆን የሚሠ ራውም ከቆዳ ሲሆን፤ የእመቤታችን ምሳሌ ነው።።